## የአረጋውያን የህግ ፕሮጀክት ምንድን ነው?

የአረጋውያን የህግ ፕሮጀክት (SLP) በመልትኖማህ ካውንቲ የአረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአርበኞች አገልግሎቶች የሚደገፍ እና በኦሪገን የህግ ድጋፍ አገልግሎቶች የሚተዳደር የበጎ ፈቃደኛ የህግ ጠበቃ መርሃግብር ነው።

የበጎ ፈቃደኛ ጠበቆች በመልትኖማህ ካውንቲ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ ዘጠኝ የአረጋውያን ማእከሎች ውስጥ ለአረጋውያን የ 30 ደቂቃ ነጻ ቀጠሮዎችን ይሰጣሉ።

## የአረጋውያን የህግ ፕሮጀክት ጠበቃ ሊረዳኝ ይችላል?

የ SLP ጠበቆች የሪል ስቴት እቅድ፣ የሸማች ጉዳዮች፣ እና የመኖሪያ ቤት ችግሮች በመሳሰሉት የፍትሐ ብሔር ህግ ጉዳዮች ላይ ደንበኞችን ይረዳሉ። የ SLP ጠበቃ ሊረዳዎት እንደሚችል እና እንደማይችል ለማወቅ ከፈለጉ በአካባቢዎ ወደሚገኘው የአረጋውያን ማእከል ይደውሉ።

የሚከተሉትን የሚያሟሉ ከሆነ ከበጎ ፈቃድ ጠበቃ ጋር የ 30 ደቂቃ ቀጠሮ ለማግኘት ብቁ ነዎት፥

- እድሜዎ 60 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ፣ ወይም የትዳር አጋርዎ እድሜ 60 ዓመት ወይም ከዛ በላይ ከሆነ፣
- በመልትኖማህ ካውንቲ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ወይም በመልትኖማህ ካውንቲ ውስጥ የህግ ጉዳይ ካለዎት፣ እና
- የዩ.ኤስ. ዜጋ ወይም ህጋዊ ነዋሪ ከሆኑ። ለቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎች የተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## LASO ን ያግኙ

የኦሪገን ሕግ ድጋፍ አገልግሎቶች
የፖርትላንድ ክልል ጽ/ቤት
520 SW 6th Ave., Suite 700
Portland, OR 97204
**ስልክ፥** 503-224-4086
**ፋክስ፥** 503-295-9496

## ስለ LASO ተጨማሪ መረጃ

LASO የፍትሐ ብሔር (ወንጀል ነክ ያልሆኑ) ጉዳዮችን ብቻ ያስተናግዳል። የ LASO ጠበቆች የመኖሪያ ቤቶች፣ ከቤት ማስወጣት፣ ቤት መውረስ/ፎርክሎዠር፣ በአረጋውያን ላይ የሚደርስ ጥቃት፣ እንክብካቤ መስጠት፣ የቤተሰብ ህግ፣ ኪሳራ እና የእግድ ትዕዛዝ ጉዳዮች ላይ የህግ ድጋፍ ይሰጣል። ለነጻ የህግ ድጋፍ አገልግሎቶቻችን ብቁ ለመሆን አብዛኞቹ ደንበኞቻችን በፌደራል የድህነት ገቢ መመሪያዎች መሠረት ብቁ መሆን አለባቸው።

LASO በከፊል ለፌዴራል እና ለግዛቶች ላልተከፈለ የገንዘብ ድጋፍ ነጻ የህግ ድጋፍ መስጠት ይችላል። ከዚህም ሌላ የተወሰኑ ለህብረተሰቡ ጥቅም የሚሆኑ፣ ወይም ከክፍያ ነጻ የሆኑ ጉዳዮችን ከሚቀበሉ የአካባቢ ጠበቆች ጋር በጋራ እንሰራለን። ባለብን የሀብት ውስንነት የተነሳ ለሁሉም ብቁ የሆኑ የህግ ድጋፍ መስጠት አንችልም። ጉዳዮችን የምንቀበለው በሰራተኞቻችን የመገኘት ሁኔታ፣ በጉዳይዎ ጥንካሬ፣ እና ጉዳይዎ ቢሯችን በወቅቱ ካስቀመጣቸው ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ዝርዝር ጋር ይሄዳል ወይስ አይሄድም በሚሉት ነገሮች ላይ ተመስርተን ነው።

LEGAL AID SERVICES OF OREGON
PORTLAND REGIONAL OFFICE

# የአረጋውያን የህግ ፕሮጀክት

*ለአረጋውያን ነጻ የህግ አገልግሎት የሚሰጡ ጠበቆች*



## የፍትሐ ብሔር ህግ ጉዳዮች ላይ እገዛ ይፈልጋሉ?

እድሜዎ 60 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነና በመልትኖማህ ካውንቲ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ወይም በመልትኖማህ ካውንቲ ውስጥ የህግ ጉዳይ ካለዎት **ያህል ከበጎ ፈቃደኛ ጠበቃ የ 30 ደቂቃ የምክር አገልግሎት በነጻ ማግኘት ይችላሉ።**

## የ 30 ደቂቃው ቀጠሮው ምን ያህል ክፍያ ያስከፍላል?

ከበጎ ፈቃደኛ ጠበቃ ጋር ለሚደረገው የ 30 ደቂቃ ቀጠሮ ምንም ክፍያ አይኖርም።

## ቀጣይ የሆነ የህግ ድጋፍ ቢያስፈልገኝስ?

በጎ ፈቃደኛ ጠበቃው ጉዳይዎን ለመያዝ ከተስማማ እና የህግ ድጋፍ የገንዘብ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ አገልግሎቶቹ በነጻ ይሰጣሉ።

ነጻ የሆኑ ቀጣይነት ያላቸው አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ካልሆኑ እና የበጎ ፈቃደኛ ጠበቃውን መቅጠር ከፈለጉ፣ ስለ ክፍያዎቹ ከጠበቃው/ዋ ጋር መነጋገር ይችላሉ።

ሌላ ጠበቃ ለመቅጠር ከፈለጉ ለኦሪጎን ስቴት ባር ሎውየር ሪፈራል ሰርቪስ በሚከተለው ስልክ ቁጥር ይደውሉ፥ 1-800-452-7636። እነሱ በልዩ የህግ ጉዳይዎ ላይ ሊረዳዎ የሚችል ጠበቃ ስም ሊሰጡዎ ይችላሉ።

## የህግ ድጋፍ ጉዳዬን ሊቀበል ይችላል?

የኦሪገን የህግ ድጋፍ አገልግሎቶች (LASO) ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች የህግ አገልግሎት የሚሰጥ ለትርፍ ያልተቋቋመ የህግ ድርጅት ነው። የህግ አገልግሎቶች በ LASO ውስጥ ለማግኘት ምንም አይነት ክፍያ የለም፣ ነገር ግን ያሉን ግብዓቶች ውስን በመሆናቸው ሁሉንም ጉዳዮች አንቀበልም።

LASO በአረጋውያን ህጎች ዙሪያ ብቃት ያላቸው ጠበቆች ያሉት ሲሆን፣ በአረጋውያን መንከባከቢያ ቤቶች፣ በአዋቂ የማደጎ ቤቶች፣ በእገዛ የሚኖርባቸው የመኖሪያ ተቋማት፣ የመኖሪያ ቤት፣ በቤት ውስጥ እንክብካቤ ሜዲኬይድ፣ ሜዲኬር፣ በአረጋውያን ላይ የሚደርስ ጥቃት፣ እና አሳዳጊዎች በመሳሰሉት ላይ ድጋፍ ይሰጣሉ። ከእነዚህ ከተጠቀሱት ጉዳዮች በአንዱ ላይ እገዛ የሚፈልጉ ከሆነ ለ LASO በስልክ ቁጥር 503-224-4086 ይደውሉ።

## ወደ ቀጠሮዬ ስመጣ ምን ይዤ መምጣት አለብኝ?

ካጋጠመዎት የህግ ጉዳይ ጋር የሚዛመድ ማንኛውንም የጽሑፍ ሰነድ ይዘው ይምጡ። እነዚህ ሰነዶች ደብዳቤዎችን፣ ፎቶ ግራፎችን፣ ህጋዊ ሰነዶችን ወይም ኢሜይሎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።



## ቀጠሮ መያዝ የምችለው እንዴት ነው?

የ SLP የህግ ተቋም የጊዜ ሰሌዳ ከዚህ በታች ተዘርዝሯል፥ ቀጠሮ ለመያዝ ለእርስዎ ወደሚያመቸው ማእከል ይደውሉ።

**YWCA/ East County**
600 NE 8th St, Room 100
Gresham, OR 97030
(503) 721.6771
*2 ኛ እና 4ኛ አርብ ከ 1 - 4 pm*

**Friendly House**
**1737 NW 26th Ave**
Portland, OR 97209
(503) 224-2640
*1 ኛ እና 3ኛ ሃሙስ ከ 9 am - ምሳ ሰዓት*

**Hollywood Senior Center**
1820 NE 40th
Portland, OR 97212
(503) 288-8303
*ዘወትር አርብ ከ 9 am - እኩለ ቀን*

**IRCO**
740 SE 106th
Portland, OR 97216
(503) 484.6371
*ዘወትር ሃሙስ ከ 1 - 4 pm*

**NAYA**
5135 NE Columbia
Portland, OR 97218
*2 ኛ እና 4ኛ ሃሙስ ከ 9 am - እኩለ ቀን*
ቀጠሮ ለመያዝ ወደ NAPOLS
በሚከተለው ስልክ ይደውሉ
(503) 223-9483

**Neighborhood House**
7688 SW Capitol Hwy
Portland, OR 97219
(503) 244-5204
*2 ኛ እና 4ኛ ማክሰኞ ከ 9 am - እኩለ ቀን*

**North Senior Services**
9009 N. Foss
Portland, OR 97217
(503) 288-8303
*1 ኛ እና 3ኛ ማክሰኞ ከ 9 am – እኩለ ቀን*

**Impact NW SE Portland**
4610 SE Belmont
Portland, OR 97215
(503) 721.6760
*ዘወትር እሮብ ከ 10 am - 1 pm*

**Urban League Multi-Cultural Senior Center**
5325 NE MLK Blvd
Portland, OR 97211
(503) 280-2600
*2 ኛ፣ 3ኛ 4ኛ ማክሰኞ ከ 1-4 pm*